የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፫ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 24
ADDIS ABABA May 21st 2010

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፸፯/፪ሺ፪
የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ገጽ ፭ሺ፪፻፷

## CONTENTS

Regulation No.177/2010
Information Technology Park Corporation
Establishment Council of
Ministers Regulation …… Page 5260

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፯/፪ሺ፪
## የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፯/፪ሺ፪» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፭. ዓላማ**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ማልማትና ማካሄድ፤ እና

፪. ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን መስጠት፡፡

## Council of Ministers Regulation No. 177/2010
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE INFORMATION TECHNOLOGY PARK CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. ***Short Title***

This Regulation may be cited as the "Information Technology Park Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 177/2010".

2. ***Establishment***

1/ The Information Technology Park Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 177/1992.

3. ***Supervising Authority***

The Ethiopian Information and Communication Technology Development Agency shall be the supervising authority of the Corporation.

4. ***Head Office***

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. ***Purpose***

The purposes for which the Corporation is established are:

1. to develop and operate information technology park; and
2. to render services related to information technology park.

**፮. ካፒታል**

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፭ ቢሊዮን (አምስት ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፬ ቢሊዮን ፪፻ሚሊዮን (አራት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል።

**፯. ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

**፰. ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

**፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፫ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**6. *Capital***

The authorized capital of the Corporation is Birr 5,000,000,000 (Five Billion Birr) of which Birr 4,200,000,000 (Four Billion Two Hundred Million Birr) is paid up in cash and in kind.

**7. *Liability***

The Corporation shall not be liable beyond its total assets.

**8. *Duration of the Corporation***

The Corporation is established for an indefinite duration.

**9. *Effective Date***

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 21st day of May 2010.

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት